# ሚዲያ... ወቅቱ የሚጠይቀው መሳሪያ!

ዳዊት ከበደ

*ይህንን አጭር ማስታወሻ ለማዘጋጀት የተገደድኩት፤ ጊዜው ሚዲያ የሚያስፈልግበት ወሳኝ ወቅት መሆኑን ከበርካታ ሰዎች ጋር ከተነጋገርኩ በኋላ ነው። በዚህ ዝርዝር ጽሁፍ ውስጥ የሚዲያ እና የድርጅትን ግንኙነት ለማንሳት እሞክራለሁ። እንደ እውነቱ ከሆነ፤ ባሁኑ ወቅት በርካታ ሚዲያዎች ወይም ድርጅቶች ሊኖሩ ይችላሉ። በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ግን "ድርጅት" ስል፤ ህዝብ የደገፈው "ቅንጅት" ማለቴ መሆኑ ግልጽ ይሁን።*

November 2, 2007

ይህንን አስመልክቶ ያናገርኳቸው ወይም ያናገሩኝ ሰዎች የሚዲያን አስፈላጊነት ቢያምኑም፤ ነገር ግን "ምን አይነት ሚዲያ ያስፈልገናል?" በሚባለው ሃሳብ ላይ ግልጽ የሆነ አቀጣጫ የላቸውም። ስለሆነም ከዚህ በታች በአጭሩ የምገልጻቸው የሚዲያ ጉዳዮች፤ ጊዜያዊ ብዥታዎችን ያጠሩልናል የሚል እምነት አለኝ።

ፍጹም ነጻ የሆኑ ሌሎች ሚዲያዎችን ወደጎን በማድረግ፤ ህዝባዊ አገልግሎት የሚሰጡትን እንመለከታለን። እነሱም ሚዲያዎች በሶስት ይከፈላሉ።

1- ነጻ ሚዲያ
2- የድርጅት ልሳን
3- ከፊል ነጻ ናቸው።

## 1ኛ - ነጻ የሆኑ ነገር ግን ብዙሃኑን የሚደግፉ ሚዲያዎች።

ይህ አካል በራሱ ህግና ደንብ የሚተዳደር ሲሆን፤ ድርጅቱን ደግፎም ሆነ ወቅሶ ዜናዎችንና መጣጥፎችን ያቀርባል። ጥቂቶች በቦርድ የሚተዳደሩ ሲሆኑ፤ አብዛኛዎቹ ግን በግለሰቦች ጥረት የሚሰሩ ናቸው።

እነዚህ ሚዲያዎች ከማንኛውን ድርጅት ጋር ያልወገኑ፤ ወይም የሌላ አካል ተጽእኖ የሌለባቸው፤ ነገር ግን በባህሪያቸው ህዝባዊ የሆኑ፤ ህዝብ የተከተለውንና ህዝብ የደገፈውን፤ ወይም ለህዝብ የቆሙ ድርጅቶችን የሚደግፉ ናቸው። እነዚህ ሚዲያዎች የድርጅቱን አላማዎች ወደ ህዝቡ ለማስተላለፍ የሚረዱ እጅግ ጠቃሚ መገናኛዎች መሆናቸው ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይሆንም።

<u>ምሳሌዎች</u> - ነጻ የሆኑ ነገር ግን የድርጅቱ አጋር ሚዲያዎች በርካታ ናቸው። ጥቂቶቹን ግን መግለጽ ያስፈልጋል። በውጭ ከሚገኙ ድረ ገጾች መካከል፤ ኢትዮጵያን ሪቪው፣ ኢ.ኤም.ኤፍ፣ ኢትዮ-ሚዲያ፣ አዲስ ቮይስና ሌሎችም ይጠቀሳሉ። ከሬዲዮኖች መካከል ደግሞ የስዊድን የኢትዮጵያ ድምጽ፣ መብትና አዲስ ድምጽ ጥሩ ምሳሌ ሊሆኑ ይችላሉ።

<u>ጠቀሜታው</u> - እንዲህ ያሉ ሚዲያዎች በብዛት መፈጠራቸው ጠቀሜታው የላቀ ነው። መረጃዎች በተፈለገው መጠን ከሁሉም አቅጣጫ እንዲፈሱ አይነተኛ ሚና ይጫወታል። ከምንም በላይ "ሃሳብን በነጻነት የማስተላለፍ" መብትን በህብረተሰቡ ውስጥ ያሳድጋሉ። ይህም ለዲሞክራሲያዊ ግንባታ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

<u>ጉዳቱ</u> - ይህ አይነቱ ሚዲያ በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት የማግኘት እድሉ ከፍተኛ ነው። ስለሆነም እንዲህ ያለ ሚዲያ በድርጅቱ ላይ የሰላ ሂስ ወይም ተቃውሞ በሚያቀርብበት ወቅት፤ በድርጅቱ ላይ መጠነ ሰፊ ጉዳት ሊፈጥር ይችላል።

መደረግ የሚገባው - እንዲህ አይነቶቹን ሚዲያዎች ማበረታታት ያስፈልጋል። የቢሮ ሃላፊዎች ወይም ቃል አቀባዮች፤ ከሚዲያ ከአዘጋጆቹ ጋር በቅርበት መነጋገር ይኖርባቸዋል። መግለጫዎችን በወቅቱ መላክ ያስፈልጋል። እነዚህን ሚዲያዎች በጋዜጣዊ መግለጫዎች (የስልክ ጉባዔዎች ላይ) መጥራትና መግለጫ መስጠት ያስፈልጋል። ከዚያ ውጪ ግን በገንዘብ መደጎም ወይም ምስክር ወረቀት መስጠት፤ ብዙዎቹ ከቆሙለት ስነ-ምግባር አንጻር ፈጽሞ ትክክል አይሆንም።

## 2ኛ - የድርጅት ልሳኖች

የድርጅት ልሳኖች በቀጥታ የድርጅቱን አቋሞችና ስራዎችን የሚያስተጋቡ ናቸው። የሚተዳደሩት ድርጅቱ በሚያዘጋጀው ደንብ ነው። አዘጋጆቹ ለድርጅቱ ያላቸው ታማኝነት ተመዝኖ፤ ለዲስፕሊን ተገዢ መሆናቸው ተረጋግጦ የሚመረጡ ናቸው። ተጠሪነታቸውም ድርጅቱ ለሚወክለው አካል ሲሆን፤ የሚያሰናብታቸውም የወከላቸው ይከው አካል ይሆናል።

<u>ምሳሌዎች</u> - የሚጠቀሱ ሚዲያዎች - በአገሪቱ ህግም የማይደገፍ ስለሆነ፤ ቅንጅት በአገር ቤትና በውጭ አገር የራሱ ልሳን የሆነ፤ ወይም በዚያ ደረጃ የሚጠቀስ ሬዲዮ የለውም። ሆኖም ከድረ ገጾች መካከል "ቅንጅት ኢትዮጵያ" በዋናነት ተጠቃሽ ነው።

<u>ጠቀሜታው</u> - የድርጅቱ ደጋፊዎች፤ ያልተዛባና ቀጥተኛ የሆነ የድርጅቱን መግለጫዎች ሊያገኙበት ይችላሉ። የድርጅቱ ማኒፌስቶ፣ እቅዶች እና አቅጣጫ ጠቋሚ ትንታኔዎች በዚህ ድረ ገጽ ላይ ይስተናገዳል። ይህንን በነጻ ሚዲያዎች ላይ ለማቅረብ አዘጋጆች ግዴታ ውስጥ ስለማምይገቡ፤ አንዳንዴም ስለማያስተናግዱ፤ ድርጅቱ የሚያወጣቸውን ማናቸውም አቋሞች የሚሳውቅበት አማራጭ መድረክ መኖሩ ጠቃሚ ነው።

<u>ጉዳቱ</u> - አንደኛውና ዋነኛው ጉዳት፤ ቁጥብና ውሱን መሆኑ ነው። የሚተላለፉ መረጃዎችና መግለጫዎች ከድርጅቱ

አቋም የሚመነጩ ናቸው። ከዚህ ውጪ የሚተላለፉ ዝግጅቶች፤ ከድርጅቱ አቋም ውጪ የሆኑ ከሆነ፤ በድርጅቱ ላይ የሚደርሰው አደጋ ከፍተኛ ነው። በዚህም መሰረት ቁጥብ ለመሆን ይገደዳል።

ሌላው ጉዳት ደግሞ ውሱንነቱ ነው። የሚያተኩርባቸው ጉዳዮች ውሱን እንደመሆናቸው መጠን፤ ታዳሚዎቹ (ታርጌት ኦዲየንሱ) በተወሰነ ክልል ደረጃ ውስጥ ያለው ብቻ ነው የሚሆነው። ሌላው ቀርቶ፤ ቃለ ምልልስ ለማድረግ ቢያስፈልግ እንኳን በርካታ ምሁራን ወይም ሰዎች በፖለቲካ ድርጅት ልሳን ላይ መቅረብ በቀጥታ የድርጅቱ አባል እንደሆኑ ስለሚያስቆጥርባችው ለመቅረብ ፈቃደኛ አይሆኑም። ይህም መላውን ህዝብ የማያሳትፍ ይሆንና በሂደት ከመጎልበት ይልቅ፤ የመቀጨጭ አደጋ ሊጋረጥበት ይችላል።

ከዚያ ውጪ የፓርቲ ልሳን መሆኑ ያልለየለት፤ ነገር ግን ሙሉ በሙሉ በፓርቲ ሰዎች የሚያዙ ሚዲያዎችን ጉዳት ትንሳኤ ሬዲዮን ምሳሌ በማድረግ መጥቀስ ይቻላል። የልዩነት አደጋ ሲጋረጥ ለአንደኛው አካል በግልጽ በመወገን፤ የሌላውን ወገን ሰዎች ከሪፖርተሮች ጀምሮ አዘጋጆቹን ጭምር እስከማግለል ደረጃ ሊደረስ ይችላል። ቅንጅት ላይ ያጋጠመው አይነት ልዩነት ሲፈጠር፤ ጉዳዩን ለድርጅቱ ከመተው ይልቅ፤ አንዱን ወገን በመያዝ ሊመጣ የሚችለውን አደጋ ከትንሳኤ ሬዲዮ መማር ይቻላል።

መደረግ የሚገባው - የድርጅት ልሳን የሆነ ሬዲዮ መመስረት ስራውን አድካሚ፤ የፋይናንስ ወጪውንም ብዙ ያደርገዋል። በሬዲዮ ረገድ፤ ጥቅምና ጉዳቱን በመመዘን ወቅታዊ ውሳኔ መስጠት ይቻላል። ከዚያ ውጪ ግን የቅንጅት ቢሮዎች የሚጠቀሙባቸው፤ ዴዲኬትድ ሰርቨሮች በውጭ አገር ማኖር አስፈላጊ ነው። አንድ ድረ ገጽ ብቻ ሳይሆን፤ ከውጭ ድርጅቶች እንደምንማረው፤ ልዩ ልዩ ዲፓርትመንቶች የሚያንቀሳቅሱት ድረ ገጽ ያስፈልጋል። የፕሬስ ውጤቶች በአገር ውስጥና በውጭ አገር መመስረት ያስፈልጋል። በዚህ አይነቱ ልሳን ላይ የሚሰሩ የድርጅቱ ሙያተኞች በክፍያ ወይም በጊዜያዊ ማበረታቻ መስራት አለባቸው።

## 3ኛ - ከፊል ነጻ የሆኑ ሚዲያዎች።

ነጻ የሆኑ ሚዲያዎች በባህሪያቸው በቁጥር አንድ ላይ ከተጠቀሱት ጋር ይመሳሰላሉ። የሚለያቸው ነገር ቢኖር፤ በሚይዙት የሰው ብዛትና ስብጥር ይሆናል። በግለሰቦች ፍላጎት ሳይሆን፤ በጋራ ውሳኔ የሚደረስባቸውን ስምምነቶች መሰረት በማድረግ ስራቸውን ይከውናሉ። የበላይ አካል ሆኖ ድርጅቱን በገንዘብና በህግ የሚያስተዳድር ቦርድ ይኖራል። ቦርዱም ታዋቂ ሰዎች፣ የድርጅቱ ሰዎችና ሙያተኞችን የሚያካትት ይሆናል። ከዚህ ቦርድ ውስጥ ሙያተኞች ተነጥለው ወጥተው፤ ኤዲቶሪያል ቦርድ ያቋቁማሉ። የየእለቱንም ስራ ይህ ኤዲቶሪያል ቦርድ ያከናውናል።

ዋናው ቦርድ የሚሰበሰበው ህግና ደንብ ለማውጣት፣ ምርጫ ለማድረግ፣ የፋይናንስ ሪፖርት ለማድረግ ወይም ገንዘብ ለመፍቀድ ሁሉንም አባላት ሰብስቦ መወያየት ይችላል። አልፎ አልፎም የሚዲያ ድርጅቱን በተመለከተ ያጋጠሙ ችግሮችን ለመፍታት ወይም ከሚዲያ ፖሊሲው ውጪ ድርጅቱን አደጋ ላይ የሚጥሉ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ሊሰበሰብ ይችላል። ከዚያ ውጪ ግን የሚዲያውን ስራ ሙሉ ለሙሉ፤ በነጻነት የሚሰሩት የኤዲቶሪያል አባላት ይሆናሉ።

<u>ምሳሌዎች</u> - እዚህ ላይ እንደ ምሳሌ መጥቀስ የሚቻለው፤ የአሁኑን ሳይሆን፤ የቅንጅት መሪዎች ከመፈታታቸው በፊት የነበረውን ትንሳኤ ሬዲዮ ይሆናል። አሁን ያለበት ሁኔታ ግን እዚህ ላይ ምሳሌ ሆኖ መቅረብ አይችልም። ምናልባት ኢ.ቲ.ኤን ቴሌቪዥን የተሻለ ምሳሌ ሆኖ ሊጠቀስ የሚችል የሚዲያ ድርጅት ነው።

<u>ጠቀሜታው</u> - በከፊል ነጻ ሆኖ የሚቋቋም የሚዲያ አካል ጠቀሜታው ለድርጅቱም ሆነ ለህብረተሰቡ ነው። ተቆጣጣሪ ያለው በህግ የሚመራ፤ የሰለጠነ አሰራርን መሰረት ያደረገና ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ፤ ትልቅ ተቋም መመስረት ይቻላል። በባህሪው የህዝብ ድምጽ ሆኖ ስለሚያገለግል፤ በአገር ውስጥ ድምጽ ለተነፈጉ የፖለቲካ ድርጅቶች አማራጭ ድምጽ ይሆናቸዋል። በአገር ውስጥና በውጭ አገር ሰፊ የሆነ የመረጃ መረብ ለመዘርጋት ያስችላል። የህዝቡንም ቅሬታና ትችት በነሳነት ያስተናግዳል። በመሆኑም አድማጮቹ በርካታ ይሆናሉ። ቃለ ምልልስ ከመስጠት ጀምሮ፤ በፋይናንስና በምክር በመደገፍ ረገድም ሰፊ ተሳታፊ ሊኖረው ይችላል።

<u>ጉዳቱ</u> - የእንደዚህ አይነት ትላልቅ የሚዲያ ተቋማት መፈጠር፤ ትናንሾቹን ወይም የግል ሚዲያዎችን ያቀጭጨቻቸዋል።

መደረግ የሚገባው - እንደዚህ አይነቱን በከፊል ነጻ የሆነ የሚዲያ ተቋም ከሙያተኞች፤ ወይም በግል ሚዲያዎችን ከሚያስተዳድሩ ግለሰቦች ጋር በመሆን መጀምር ይገባል። በውጭ አገር በህጋዊ መንገድ በመመዝገብ፤ ሁሉም በእኩል ተደማምጠው ለአንድ አላማ ሊሰሩበት የሚገባ መድረክ መፍጠር ያስፈልጋል። ይህም ማለት የፖለቲካ ድርጅት የሚቆጣጠረው ሳይሆን አካል መፍጠር እንዳልሆነ ግልጽ መሆን አለበት።

በአጠቃላይ ድርጅቱ በውጭ ከሚገኙ ሙያተኞች ጋር በመተባበር፤ ከዘመኑ ስልጣኔ ጋር ወደፊት መገስገስ ይኖርበታል። የኢንተርኔት ሬዲዮና አነስተኛ ማተሚያ ቤቶች ያስፈልጉታል። ኢንተርኔት ካፌ ማቋቋም አለበት። ከምርጫው ወቅት በፊት እነዚህ ጉዳዮች ተገቢ ጥናት ተደርጎባቸው፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተፈጻሚ መሆን ወቅቱ የሚጠይቀው ግዴታ ይሆናል። ይህም ለነገ የምናስቀምጠው ሳይሆን፤ ዛሬ ጀምረን ነገ መጨረስ ያለብን ጉዳይ ነው።

አላማውን "መረጃ ኃይል ነው" ብሎ የሚንቀሳቀስ አካል አሸናፊነቱ አያጠራጥርም ❑